# የፕሮጀክት አጠቃላይ መግለጫ

## የ23ኛ ጎዳና የኮሪደር ማሻሻያዎች ፕሮጀክት

የ 2013 ክረምት

### የፕሮጀክት መግለጫ

ከ2014 የመፀው ወቅት ጀምሮ፣ የሲያትል ትራንስፖርት መምሪያ (SDOT) በ23ኛ ጎዳና ላይ የኮሪደር ማሻሻያዎችን ግንባታ ለመጀመር አቅዷል፡፡ ፕሮጀክቱ በሶስት ምዕራፎች የተከፋፈለ ሲሆን በውስጡ የሚያካትታቸው ስራዎችም የመንገድ ንጣፍ ማስተካከል፣ የትራፊክ ምልክቶችን ደረጃ ማሻሻል እና ትረንዚት፣ እግረኞች እና የብስክሌት ጋላቢዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ሌሎች የማሻሻያ ስራዎችን ነው፡፡ SDOT የ 22 ሚሊዮን ዩኤስ ዶላር በጀት አግኝቷል፤ ይሁን እንጂ፣ ለምዕራፍ 2 እና 3 የታቀዱ የማሻሻ ስራዎችን ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ገንዘብ በማፈላለግ ላይ ነን፡፡

ከፕሮጀክቱ ጠቀሜታዎች መካከል፡

- አዲስ የመንገድ ንጣፍ
- የእግረኛ መንገድ ማሻሻያዎች
- የመንገድ ሙብራት ማሻሻያ ስራዎች
- የትራንዚት አስተማማኝነትን ማሳደግ
- የትራፊክ ምልክት ማሻሻያዎች
- ሕዝባዊ ስነ ጥበብ

የእያንዳንዱ ምዕራፍ የዲዛይን ስራ በመካሄድ ላይ ነው፡፡ የምዕራፍ 1 ግንባታ እስከ 2014 የመፀው ወቅት ይጀመራል፡፡ ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ የሚገኝ ከሆነ፣ የምዕራፍ 2 እና 3 ግንባታ እስከ 2015 የክረምት ወቅት ይጀመራል፡፡

### አዲስ፣ ባለ ሶስት ረድፍ አቀማመጥ

የሁሉንም ተጠቃሚዎች ፍላጎት ለማጣጣምና በኮሪደር ላይ ደህንነትን ለማረጋገጥ፣ SDOT በምዕራፍ 1 እና 2 ላይ ባለ ሶስት ረድፍ የመኪና ጎዳና አቀማመጥ ዲዛይን የማውጣት ተግባር በማከናወን ላይ ነው - ነገር ግን አንዳንድ ወሳኝ የሚባሉ መስቀለኛ መንገዶች ባለ አራት ረድፍ አቀማመጥን ይዘው ይቀጥላሉ፡፡ ባለ ሶስት ረድፍ አቀማመጥ ለአሽከርካሪዎች፣ ለእግረኞች እና ለሳይክል ጋላቢዎች የደህንነት ማሻሻያዎችን የሚፈጥር ሲሆን የትራንዚት ፍጥነትና አስተማማኝነትንም ያሳድጋል፡፡



Represents the typical configuration; lane widths vary throughout the corridor

### የፕሮጀክት አድራሻ




**የፕሮጀክቱ የግንኙነት መረጃ**
ማሪቤል ክሩዝ (Maribel Cruz) የፕጀክት ግንኙነት መሪ (Project Communications Lead)
Maribel.cruz@seattle.gov, (206) 684-7963

ለተጨማሪ የተተረጎመ መረጃ፣ እባክዎ በዚህ ቁጥር ይደውሉ፡ (206) 733-9990፡፡

BRIDGING the GAP
SDOT Seattle Department of Transportation